SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

# ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

# DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

# OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር
ወላይታሶዶ ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No
Wolaita Sodo , 2024

## ደንብ ቁጥር -4 /፳፻፲7 ዓ.ም

## የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ክልላዊ የፍልሰት ምክር ቤት እና የትብብር ጥምረት ለማደራጀትና የአሰራር ስርዓት ለመወሰን የወጣ ደንብ

መግቢያ

በፌዴራል መንግስት ደረጃ በሰዎች የመነገድ እና ሰውን በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ዓላማ ማስፈጸሚያ እንደየክልሉ ነባራዊ ሁኔታ አግባብነት ያላቸውን አካላት ያቀፈውን የፍልሰት ፍልሰት ምክር ቤት ፣ የትብብር ጥምረትንና በሥሩ የሥራ ቡድኖችን አደረጃጀት ማቋቋም እንደሚያስፈልግ የተደነገገ በመሆኑ፤

በክልሉ በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠርን የፍልሰት ፍልሰት ምክር ቤት እና የትብብር ጥምረት መካከል የሚኖረውን ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከርና ተደራሽነትን በማስፋት አደረጃጀቶች በሪጅዮፖሊስ ከተሞች፣በዞን፣ በከተማ አስተዳደር፣ ወረዳ እና ቀበሌ መዋቅሮች ድረስ ማውረድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በክልሉ በሰዎች የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀሎች አማካኝነት ለጉዳት የሚዳረጉ ተገጂዎችን ለማዳን እርዳታ ማሰባሰብ፣ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ እና መልሶ ማቋቋም ረገድ በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የላቀ ተሳትፎ እና ቅንጅታዊ አሰራርን ለማጠናከር ክልላዊ የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከክልሉ ወደ ውጭ ሀገር የሥራ እድል ፍለጋ የሚሄዱ ዜጎቻችን ህገወጥ መንገድን ተመራጭ እንዳያደርጉና በዚህ ምክንያት በጉዞ ላይ እና በተቀባይ ሀገር የሚደርስባቸውን እንግልት፣ መከራና ሞት እንዲሁም የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለመከላከል ህጋዊውን መንገድ ብቻ እንዲከተሉ ለማበረታታትና በምክር መደገፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ፍልሰት ምክር ቤት በክልሉ አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋም ፣ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 3/2015 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በሰዎች የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 33 (5) እና 35 (5) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ክልላዊ የፍልሰት ምክር ቤት እና ትብብር ጥምረት ለማደራጀትና የአሰራር ስርዓት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር -4 /፳፻፲7" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

1) “አዋጅ” ማለት በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና ሰውን ሕገወጥ መንገድ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ያወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ነው፤

2) “ቢሮ" ማለት የትብብር ጥምረት ጽ/ቤት የሚገኝበት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ ነው፤

3) “ክልላዊ ምክር ቤት ” ማለት አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 33 (5) መሰረት በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በሕገ-ወጥ መንገድ ለስራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣ አዋጅ እና በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ ክልላዊ ምክር ቤት ነው፤

4) “ክልላዊ ትብብር ጥምረት” ማለት አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 35 (5) መሰረት በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በሕገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ መላክ ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ እና በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ ክልላዊ ትብብር ጥምረት ነው፤

5) “ፍልሰት” ማለት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረግ የሰው ወይም የሰዎች እንቅስቃሴ ስሆን ስደተኞችን፣ የተፈናቀሉ ሰዎችን፣ የኢኮኖሚ ፍልሰተኞችን የሚያመለክት ስሆን በአጠቃላይ በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ በሆኑ ምክንያቶች የሚደረግ እንቅስቃሴን ያጠቃልላል፤

6) “ተጎጂ" ማለት በዚህ በአዋጅ ቁጥር 1178/12 ከተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች አንድ ወይም ከአንድ በላይ የተፈፀመበት እና አካላዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የደረሰበት ወይም የመብት ጥሰት የተፈፀመበት ወይም እነዚህ ጉዳቶች የደረሱበት ወይም የመብት ጥሰት የደረሰበት ባይሆንም ለወንጀሉ የተጋለጠ ወይም ሊጋለጥ የሚችል በመሆኑ በዚህ አዋጅ የተመለከተው ጥበቃና ድጋፍ እንደአግባብነቱ የሚያስፈልገው ሰው ነው፤

7) “የሥራ ቡድን” ማለት በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በሕገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትብብር ጥምረት ስር የተዋቀረ የሥራ ቡድን ነው፤

8) “ዞን” ማለት በክልሉ መንግስታዊ የስልጣን አወቃቀር መሰረት ሁለተኛ እርከን ላይ የሚገኝ የመንግስት አደረጃጀት ነው፤

9) “ወረዳ” ማለት በክልሉ መንግስታዊ የስልጣን አወቃቀር መሰረት ሶስተኛ እርከን ላይ የሚገኝ የመንግስት አደረጃጀት ነው፤

10) “ቀበሌ” ማለት በክልሉ መንግስታዊ የስልጣን አወቃቀር መሰረት ከወረዳ ቀጥሎ ታችኛው እርከን ላይ የሚገኝ የመንግስት አደረጃጀት ነው፤

11) “የከተማ አስተዳደር” ማለት ተለይቶ በታወቀ ወሰን የተደራጀ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥን ለመምራት ሥልጣንና ኃላፊነት በህግ የተሰጠው ከተማ ነው፤

12) “የስር ተቋማት ወይም በየደረጃው የተቋቋሙ ተቋማት" ማለት የዞን፣የከተማ አስተዳደር፣ የወረዳ እና ቀበሌ የመንግስት ስልጣን መዋቅር በአባል ተቋማት የያዘ ክልላዊ የትብብር ጥምረት አደረጃጀት ማለት ነው፤

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

13) በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 2 እና በህገወጥ የሰዎች ዝውውር ጉዳዮች ጋር ተያይዞ በወጡ ሌሎች አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደየአግባብነታቸው ለዚህ ደንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ ደንብ ወስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

አንቀጽ 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በክልላዊ የፍልሰት ምክር ቤት አባል ተቋማት፣በሪጅዮፖሊስ ከተሞች፣ በዞን፣ በከተማ አስተዳደር፣ በወረዳ እና በቀበሌ ባለው ክልላዊ የትብብር ጥምረት አባል ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

## ክፍል ሁለት

### ስለ ክልላዊ የፍልሰት ምክር ቤት መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ አደረጃጀት እና ተግባርና ኃላፊነት

አንቀጽ 5. ስለ ፍልሰት ምክር ቤት መቋቋም እና ተጠሪነት

1) በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና ሰውን ሕገወጥ መንገድ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልል ደረጃ አስተባባሪ ምክር ቤት ከዚህ በኋላ "ክልላዊ ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

2) በክልል ደረጃ የሚቋቋመው ክልላዊ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል፤

3) ክልላዊ ምክር ቤት ሰብሳቢ የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሲሆን ምክትል ሰብሳቢው ፍትህ ቢሮ ኃላፊ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 6. ክልላዊ ምክር ቤት አደረጃጀት

1) ክልላዊ ምክር ቤቱ በክልል ደረጃ በሰዎች መነገድና ሰዎችን ህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር እና ሰዎችን ህገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀሎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚከተሉትን ተቋማት በአባልነት ይዞ ተደራጅቷል፡፡

ሀ/ የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የፍልሰት ፍልሰት ምክር ቤት …… ሰብሳቢ፤

ለ/ የክልሉ ፍትሕ ቢሮ……………………………………ምክትል ሰብሳቢ

ሐ/ የክልሉ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ———————————ፀሐፊ

መ/ የክልሉ ሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ……………አባል

ሠ/ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ………………………………………………አባል

ረ/ የክልሉ ሰላምና ፀጥታ ቢሮ……………………………………………አባል

ሰ/ የክልሉ ጤና ቢሮ …………………………………………………….አባል

ሸ/ የክልሉ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ………………… አባል

ቀ/ የክልሉ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ…………………………………….አባል

በ/ የክልሉ ሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ቢሮ ……………………………….አባል

ተ/ የክልሉ ትምህርት ቢሮ………………………………………………አባል

ቸ/ የክልሉ ኢንቨትመንት ቢሮ ………………………………… አባል

ነ/ የክልሉ ግብርና ቢሮ………………………………………………አባል

ኘ/ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ …………………………………….አባል

አ/ የክልሉ ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ ……………………….አባል

ከ/ የክልሉ ኮሙኒኬሽን ቢሮ………………………………… አባል

ኸ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት…………………………….አባል

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

ወ/ የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ………………………… አባል

ዐ/ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት―――――――አባል፤

ዘ/ የክልሉ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ …………………….…አባል

ዠ/ ሕዝባዊ አደረጃጀቶች፤ እና

2) እንደአግባብነቱ በሰብሳቢ እንዲካተቱ የሚደረጉ ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን ያቀፈ ይሆናል፡፡

3) ተቋማት በክልላዊ ምክር ቤት በኃላፊዎች ወይም ምክትል ኃላፊዎች የሚወከሉ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 7. ክልላዊ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

ክልላዊ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፦

1) በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በሕገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ስትራቴጂያዊ እቅድ ያቅዳል፤ አፈጻጸሙን ይገመግማል፤ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤

2) የክልላዊ ትብብር ጥምረት የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅዶች እና መርሃ ግብር አፈጻጸሙን ይገመግማል፤

3) ክልላዊ የትብብር ጥምረት ለስራው የሚሆን ዓመታዊ የበጀት ዕቅድ ሲያቀርብ ገምግሞ ተገቢው በጀት እንዲፀድቅ ያደርጋል እንዲሁም ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የበጀት ድጋፉ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፤

4) ለክልላዊ ትብብር ጥምረት የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

5) ተጎጂዎችን ማዳን፣ መልሶ ማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበትና ከህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት እና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ ክልል አቀፍ የቅብብሎሽ ስርዓት መመሪያ እንዲወጣ ያደርጋል፤ ያፀድቃል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

6) በሰዎች የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር እና በሕገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀል ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና ምላሽ ስለሚደረግበት፣ የሥራ ዕድል ስለሚፈጠርበትና መሰል ጉዳዮች ተግባራዊ ስለሚደረጉበት ሁኔታ ምክረ-ሀሳብ ያቀርባል፣ እነዚህ ጉዳዮች ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸው ተቋሞች ተግባራቸውን ስለመፈጸማቸው ይከታተላል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

7) የውስጥ አሰራሩን ለማጠናከርና ከክልል የትብብር ጥምረቱ ጋር ስለሚኖረው የአሰራር ግንኙነት ጋር በተያያዘ መመሪያ እንዲወጣ ያደርጋል፤

8) ከፌዴራል ብሔራዊ ፍልሰት ምክር ቤት ና ትብብር ጥምረቶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

9) ከክልሉ ከስር ተቋማት ክልላዊ ትብብር ጥምረት አደረጃጀቶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

10) ከብሄራዊ ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 8.የክልላዊ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

1) በዚህ ደንብ መሰረት ለክለሉ ምክር ቤት የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፤
2) የክልላዊ ምክር ቤቱን ስብሰባዎችን ይመራል፤
3) አስቸኳይ ስብሰባዎችን ይጠራል፤
4) ክልላዊ ምክር ቤት በመወከል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤
5) ለክልላዊ ምክር ቤቱ ተጠሪ የሆኑ አካላት ኃላፊዎችን ይሰይማል፤
6) የክልላዊ ምክር ቤት ውሳኔ አፈጻጸም ይከታተላል፤
7) የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድና ሪፖርት ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፤
8) በየስድስት ወሩ የክልላዊ ምክር ቤት የዕቅድ ክንውን አፈጻጸም ሪፖርት ለምክር ቤቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፤
9) በክልላዊ ምክር ቤት እና በብሔራዊ ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 9. የሰብሳቢው ተጠሪነት

የክልላዊ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ተጠሪነቱ ለክልላዊ ምክር ቤትና ለክልሉ ዋና አስተዳዳሪው ይሆናል፡፡

አንቀጽ 10. የክልላዊ ምክር ቤት ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1) ሰብሳቢው በሌለበት ወይም ሰብሳቢው ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ በዚህ ደንብ ለሰብሳቢው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራትን ያከናውናል፤
2) በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመውን ክልላዊ የትብብር ጥምረትን ይመራል፤
3) በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናወናል፡፡

አንቀጽ 11. የምክትል ሰባሳቢ ተጠሪነት

የምክትል ሰብሳቢው ተጠሪነት ለክልላዊ ምክር ቤት ሰብሳቢና ለክልላዊ ምክር ቤት ይሆናል፡፡

አንቀጽ 12. ክልላዊ ምክር ቤት አባላት መብት

ማንኛውም ክልላዊ ምክር ቤት አባል:-

1) አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ለክልላዊ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ሀሳብ ማቅረብ፤
2) ለስብሰባ አጀንዳ እንዲያዝላቸው የሚፈልጉትን ሃሳብ የማሳወቅ፤
3) በክልላዊ ምክር ቤት ስብሰባ የመሳተፍና ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ፤
4) በክልላዊ ምክር ቤት የሚተላለፉ ውሳኔዎችን የማወቅ መብት ይኖረዋል፡፡

አንቀጽ 13. ክልላዊ ምክር ቤት አባላት ግዴታ

ማንኛውም ክልላዊ ምክር ቤት አባል፦

1) አዋጅን፣ ደንብን እና መመሪያዎችን የመደበኛ ስራው አካል አድርጎ የመፈጸም እና የማስፈጸም፤
2) በክልላዊ ምክር ቤቱ መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባ የመገኘት፤

3) በክልላዊ ምክር ቤቱ የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን የመፈፀም እና የማስፈፀም፤

4) በክልላዊ ምክር ቤቱ የተቀመጠውን አቅጣጫ እና ውሳኔ የመፈፀም እና የማስፈፀም፤

5) በክልላዊ ምክር ቤቱ በምሥጢር እንዲጠበቁ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች የመጠበቅ፤ እና

6) ሌሎች በክልላዊ ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ተግባራት የመወጣት ግዴታ አለበት።

አንቀጽ. 14 የክልላዊ ምክር ቤት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

የክልላዊ ምክር ቤቱ የሚከተሉትን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ይኖረዋል፡-

1) ምክር ቤቱ በስድስት ወር እና በዓመት መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

2) ማናቸውም የፍልሰት ምክር ቤት ስብሰባ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

3) የፍልሰት ምክር ቤት የስብሰባ ውሳኔ የሚያልፈው በስብሰባው ከተገኙ የፍልሰት ምክር ቤት አባላት ከግማሽ በላይ ሲደገፍ ይሆናል፤

4) በስብሰባ ወቅት ድምፅ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሃሳብ የፍልሰት ምክር ቤት ውሳኔ ይሆናል፤

5) የትብብር ጥምረት እያንዳንዱ የሥራ ቡድን በየወሩ ይሰበሰባል።

## ክፍል ሶስት

## ስለትብብር ጥምረት መቋቋም፣ተጠሪነት፣ አደረጃጀት እና ተግባርና ኃላፊነት

አንቀጽ 15. ስለየትብብር ጥምረት መቋቋምና ተጠሪነት

1) በክልል ክልላዊ የትብበር ጥምረት፣ በሪጂዮፖሊስ ከተሞች የሪጂዮፖሊስ የትብብር ጥምረት፣በዞን የዞን የትብብር ጥምረት፣ በከተማ አስተዳደር የከተማ አስተዳደር የትብበር ጥምረት፣ በወረዳ የወረዳ የትብበር ጥምረት እና በቀበሌ የቀበሌ ትብበር ጥምረት እየተባለ የሚጠራ የትብብር ትምረት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

2) የክልላዊ የትብብር ጥምረቱ ሰብሳቢ የክልል ፍትህ ቢሮ ኃላፊ ወይም እርሱ የሚወክለው ምክትል የፍትህ ቢሮ ኃላፊ ነው።

3) በሪጂዮፖሊስ ከተሞች እና በዞን ደረጃ የትብብር ጥምረት ሰባሳቢ ፍትህ መምሪያ ኃላፊ ሲሆን በከተማ አስተዳደር እና በወረዳ ደረጃ ፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊ ሲሆን በቀበሌ ደረጃ የቀበሌው የፍትህ ዘርፍ ኃላፊ ይሆናል።

4) የክልላዊ ትብብር ጥምረቱ ተጠሪነት ለክልላዊ ምክር ቤት ሲሆን የዞናዊ፣ የከተማ አስተዳር፣ የወረዳ እና የቀበሌ የትብብር ጥምረት በተዋረድ ለሚገኝ ዋና አስተዳዳር ይሆናል።

አንቀጽ 16. ስለትብብር ጥምረት አደረጃጀት

1) የትብብር ጥምረቱ የሚከተሉትን አባል ተቋማትን ያካተተ አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

ሀ/ የክልሉ ፍትሕ ቢሮ……………………..ሰብሳቢ

ለ/ የክልሉ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ——————ፀሐፊ

ሐ/ የክልሉ ሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ……………አባል

መ/ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን …………አባል

ሠ/ የክልሉ ሰላምና ፀጥታ ቢሮ……………………………………አባል

ረ/ የክልሉ ጤና ቢሮ …………………አባል

ሰ/ የክልሉ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ……………… አባል

ሸ/ የክልሉ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ………………………………አባል

ቀ/ የክልሉ ሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ቢሮ ………………………………አባል

በ/ የክልሉ ትምህርት ቢሮ……………አባል

ተ/ የክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ ……………… አባል

ቸ/ ክልሉ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ————————አባል

ነ/ የክልሉ ግብርና ቢሮ……………………………………አባል

ኘ/ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ……………………………………አባል

አ/ የክልሉ ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ ……………………………………አባል

ከ/ የክልሉ ኮሙኒኬሽን ቢሮ……… አባል

ኸ/ የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ……… አባል

ወ/ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት---------አባል

ዐ/ በክልሉ የሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት------- አባል

ዘ/ የክልሉ ፍትህ አካላት ማሰልጠኛ ተቋም--------- አባል

ዠ/ በክልል ደረጃ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ ……አባል

ደ/ የክልሉ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ …………………………አባል

ጀ/ ሕዝባዊ አደረጃጀቶች እና

2) በክልል፣በሪጂዮፖሊስ ከተሞች፣ በዞን፣ በከተማ አስተዳደር፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ እያንዳንዱ አደረጃጀት የትብብር ጥምረት ይኖረዋል፤

3) የትብብር ጥምርቱ በክልል፣በሪጂዮፖሊስ ከተሞች፣ በዞን፣ በከተማ አስተዳደር እና በወረዳ ደረጃ የጥምረቱ አባል ተቋማትን፣ የሥራ ቡድኖችን እና እንደአስፈላጊነቱ ንዑስ የሥራ ቡድኖችን የሚያካትት ነው፤

4) በክልል፣በሪጂዮፖሊስ ከተሞች፣ በዞን፣በከተማ አስተዳደር እና በወረዳ የሚገኝ የትብብር ጥምረት እንደአስፈላጊነቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱ ተቋማትን ያካተተ ይሆናል፤

5) በየደረጃው የሚገኝ የትብብር ጥምረት ሰብሳቢ እንደአስፈላጊነቱ በአባልነት እንዲታቀፉ የሚገባቸውን አካላት በትብብር ጥምረቱ ሊያካትት ይችላል፤

6) የትብብር ጥምረቱ አባል ተቋማት በየተቋሞቻቸው አግባብነት ያላቸው ምክትል ኃላፊዎችን በአባልነት

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

እንዲታቀፍ ሊያደርጉ ይችላሉ።

አንቀጽ 17. ክልላዊ የትብብር ጥምረት ተግባርና ኃላፊነት

1) በሰው መነገድ፣ሰውን ህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር እና ሰውን ህገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እና ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋም የሚያስችሉ ጥናቶችን በማጥናት፣ፖሊሲዎችን፣ስትራቴጂዎች፣ህጎችን በማዘጋጀት ለክልላዊ ምክር ቤት ያቀርባል፤አግባቢነት ባለው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
2) ተጎጂዎችን ለማዳን የሚያስችል መልሶ ለማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፎች በሚያገኙበት ሁኔታ ለማመቻቸት፣ በህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት እና ተተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የቅብብሎሽ መመሪያ እና አሰራር ስርዓት መመሪያ ያዘጋጃል በክልላዊ ምክር ቤት ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
3) በክልል ውስጥ መፈናቀል፣ ስደትና ፍልሰት፣ ስራ እድል ፈጠራና መሰል ጉዳዮችን የተመለከተ የፖሊስ፣ የህግ ወይም ስትራቴጂ ማዕቀፍ እና አሰራር ስርዓት እንዲዘጋጅ የሚመለከተው አካለ ያስተባብራል። በሚመለከተው አካል ሲፀድቀ ተግባራዊነቱን ያከታተላል፤
4) በክልሉ አማካይ ቦታዎች ወይም ችግሩ ጎልቶ በሚታዩ አከባቢዎች ለተጎጂ ዜጎች ማቆያ ማዕከል እንዲገነባ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤
5) የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ እቅድና የድርጊት መረሃግብር ያዘጋጃል ለክልላዊ ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል ተግባራዊ ያደርጋል፤
6) ለክልላዊ ምክር ቤት በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል የሚሰጡ ግብረ መልሶችን ተግባራዊ ያደርጋል፤
7) ለክልላዊ ምክር ቤት ዓመታዊ የዕቅድ ማስፈፀሚያ ፋይናንሻል በጀት እቅድ ያቀርባል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።
8) ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በበጀት እንዲደግፉ ያስተባብራል የበጀት ድጋፍ ሲገኝ በጽህፈት ቤቱ አማካኝነት ተግባራዊ ያደርጋል፤
9) ሌሎች በክልላዊ ምክር ቤት የሚሰጡ ልዩ ልዩ ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 18.በየደረጃው ስለተደራጁ የትብብር ጥምረት ኃላፊነትና ተግባር

የሪጂዮፖሊስ ከተሞች፣ የዞን፣ ከተማ አስተዳደር እና የወረዳ የትብብር ጥምረት የሚከተሉትን ኃላፊነትና ተግባር ይኖራቸዋል:-

1) በሰው መነገድ፣ሰውን ህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር እና ሰውን ህገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እና ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋም የሚያስችሉ ጥናቶችን ለማጥናት፣ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎችን ለማዘጋጀት የሚረዳ ግብአት ያቀርባል በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤
2) ተጎጂዎችን ለማዳን የሚያስችል መልሶ ለማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፎች በሚያገኙበት ሁኔታ ለማመቻቸት፣ በህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት እና ተተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የቅብብሎሽ መመሪያ እና አሰራር ስርዓት መመሪያ እንዲዘጋጅ ምክረ ሀሳብ ያቀርባሉ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

3) በክልል ውስጥ መፈናቀል፣ ስደትና ፍልሰት፣ ስራ እድል ፈጠራና መሰል ጉዳዮችን የተመለከተ የፖሊስ፣ የህግ ወይም ስትራቴጂ ማዕቀፍ እና አሰራር ስርዓት እንዲዘጋጅ ምክረ ሀሳብ ያቀርባሉ በሚመለከተው አካል ሲፀድቀ ተግባራዊ ያደርጋል። በየአካባቢ ድጋፍ እንዲገኝ የተለያዩ አካላትን ያስተባብራሉ ያሰባስባሉ የተገኘውን ድጋፍ በተግባር ላይ ያውላሉ፤

4) ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር መውጣት የሚፈልጉ ዜጎች ህጋዊ መንገድን ተከትሎ እንዲወጡ የማበረታታት እና ተገቢውን መረጃ እንዲያገኙ የማድረግ ስራ እንዲሰራ ያደርጋል ይከታተላል ድጋፊ ያደርጋል፤

5) ከበላይ የትብብር ጥምረት የወረደውን ዓመታዊ እቅድ መነሻ በማድረግ የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታዎችን ያገናዘበ እቅድ ያቅዳል ተግባራዊ ያደርጋል፤

6) እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዳ ዓመታዊ ፋይናንሻል እቅድ ለሚመለከተው ለዞን፣ለከተማ አስተዳደር እና ወረዳ መንግስት አካል በማቅረብ እንዲፈቀድ ያደርጋል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

7) የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ እቅድና የድርጊት መረሃግብር ያዘጋጃሉ በየደረጃው ለሚገኝ ትብብር ጥምረት በማቅረብ ያፀድቃል ተግባራዊ ያደርጋል፤

8) በየወቅቱ የሶስት ወር፣ የስድስት ወር እና የዓመት ሪፖርት በየደረጃው ለሚገኝ ለባላይ ትብብር ጥምረት ያቀርባሉ የሚሰጡ ግብረ መልሶችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

9) ሌሎች በየደረጃው ከሚገኝ ከበላይ ትብብር ጥምረት የሚሰጡ ልዩ ልዩ ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 19.የቀበሌ የትብብር ጥምረት አደረጃጀት፣ተጠሪነትና ኃላፊነት

1) የቀበሌ የትብብር ጥምረት በቀበሌ ደረጃ የሚገኝ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆነ መዋቅራዊ አደረጃጀትንና ተቋማትን እንደአስፈላጊነቱ ያካተተ የቀበሌ ትብብር ጥምረት አደረጃጀት ይኖረዋል።

   ሀ/ የቀበሌ ፍትህ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ተቀራራቢነት ያለው ዘርፍ..... ሰብሳቢ

   ለ/ የቀበሌ ሥ/አስኪያጅ.................. ፀሐፊ

   ሐ/ በቀበሌ የሚገኝ ት/ት ተቋም....... አባል

   መ/ በቀበሌ የሚገኝ ጤና ተቋም....... አባል

   ሠ/ በቀበሌ የሚገኝ ግብርና ተቋም...... አባል

2) ሌሎችም ለዚህ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ካሉ በሰቢሳቢው አማካኝነት ማካተት የሚቻል ይሆናል።

3) የቀበሌ የትብብር ጥምረት ተጠሪነቱ ለቀበሌው ዋና አስተዳዳር ይሆናል።

አንቀጽ 20. የቀበሌ የትብብር ጥምረት ኃላፊነትና ተግባር

1) በቀበሌ ደረጃ የሚገኝ የትብብር ጥምረት እንደ አንድ ቡድን ሆኖ በቀበሌ ውስጥ በሰዎች መነገድና ሰዎችን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀሎችን መከላከልና መቆጣጠር ሥራዎችን ይሰራል፤

2) በየደረጃው ከሚገኙ ከበላይ ትብብር ጥምረት የሚወርዱ መመሪያዎችን፣ አሰራር ሥርዓቶችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

3) በቀበሌ ደረጃ በሰዎች መነገድና ሰዎችን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀሎችን መከላከልና

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

መቆጣጠር የሚረዳ ዕቅድ ያዘጋጃል ተግባራዊ ያደርጋል፤

4) የተሰሩ ሰራዎችን በተመለከተ ለወረዳ ትብብር ጥምረት የሶስት ወር የስድስት ወር እና የዓመት የአፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል። ግብረ መልስ ሲሰጥ ተቀብሎ ተግባራዊ ያደርጋል፤
5) ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር መውጣት የሚፈልጉ ዜጎች በህጋዊ መንገድን ተከትሎ እንዲወጡ ያበረታታል ተገቢውን መረጃ እንዲያገኙ ድጋፊ ያደርጋል፤
6) በቀበሌ የወንጀል ድርጊት ተፈፀሞ ሲገኝ ለሚመለከተው ፀጥታ አካል ወዲያው መረጃ ያስተላልፋል ጉዳዩ የደረሰበትን ክትትል ያደርጋል፤
7) ተጎጂዎችን ለማዳንና ለአደጋ እንዳይጋለጡ የሚረዳ የድጋፍ ሁኔታዎችን (ምግብ፣ውሃ፣መጠለያ እና የልብስ) ያስተባብራል ድጋፍ ያሰበስባል እርዳታ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
8) ከወረዳ ትብብር ጥምረት እና ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት ተገጂዎች ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ ያደርጋል፤
9) ከወረዳ ትብብር ጥምረት እና ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
10) የሶስት ወር፣ የስድስት ወር እና የዓመት ሥራ አፈፃጸም ሪፖርት ወቅቱን በጠበቀ ሁኔታ ለወረዳው ትብብር ጥምረት ያቀርባል። የሚሰጠው ግብረ መልስ ተቀብሎ ተግባራዊ ያደርጋል።

አንቀጽ 21.ስለትብብር ጥምረቱ ጽህፈት ቤት አደረጃጀት

1) በክልል የክልሉ ፍትህ ቢሮ የትብብር ጥምረቱ ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤
2) በሪጂዮፖሊስ ከተሞች፣በዞን እና በከተማ አስተዳደር ፍትህ መምሪያ እና በወረዳ የወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት የትብብር ጥምረት ጽ/ቤት ሆኖ ያገለግላል፤
3) በሪጂዮፖሊስ ከተሞች እና በዞን ፍትህ መምሪያ ደረጃ መደበኛ ዐቃቤ ህግ ተመድቦላቸው የትብብር ጥምረት ተግባራትን የሚያከናውን ይሆናል፤
4) በከተማ አስተዳደር ፍትህ መምሪያ እና ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ደረጃ አንድ ዐ/ህግ በፎካል ፐርሰንነት ተመድቦ የሚሰራ ይሆናል፤
5) በቀበሌ ደረጃ የቀበሌ ጽ/ቤት የትብብር ጥምረት ጽ/ቤት ሆኖ ያገለግላል፤
6) በዞን ደረጃ የሚገኝ የትብብር ጥምረት ጽህፈት ቤት እንደአስፈላጊነቱ በበቂ ሰው ሃይል፣ በበጀት እና በሎጂስቲክ እንዲደገፍ ይደረጋል፤
7) በከተማ አስተዳደር እና በወረዳ ደረጃ አንድ ዐቃቤ ህግ በፎካል ፐርሰንነት ተመድቦ እንዲሰራ ይደረጋል፤
8) በቀበሌ ደረጃ የቀበለው ሥራ አስኪያጅ በፎካል ፐርሰንነት ተመድቦ እንዲሰራ ይደረጋል።

አንቀጽ 22. የክልል የትብብር ጥምረት ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

ጽህፈት ቤቱ የሚከተለው ተግባር እና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1) ክልላዊ ትብብር ጥምረት ከክልላዊ ምክር ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎች እና አቅጣጫዎች ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
2) የትብበር ጥምረት ስራዎችና ስብሰባዎች ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን የማስተባበር ሚና ይወጣል፤

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

ስብሰባዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው እንዲጠሩ ይከታተላል፣

3) በዚህ ደንብ መሰረት ለትብብር ጥምረት የተሰጡ ተግባራትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

4) የትብብር ጥምረቱንና የሥራ ቡድኖች እቅዶችና ስራዎች ከሀገራዊ አጠቃላይ ስትራቴጅዎች፣ ፖሊሲዎች፣ ከህጎችና አለማቀፍ ሰነዶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ይከታተላል እንዲሁም በሰብሳቢው ግብረ-መልስ እንዲሰጥ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፤

5) የትብብር ጥምረቱ ተሳታፊዎች በሚደረጉ ስብሰባዎችና ሌሎች መድረኮች በአግባቡ እየተሳተፉ ስለመሆኑ ክትትል ያደርጋል፤

6) በአግባቡ የማይሳተፉ ሲኖሩ ለትብብር ጥምረቱ ሰብሳቢ በማሳወቅ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ የትብብር ጥምረቱን ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፣

7) በየደረጃው ከሚገኙ ትብብር ጥምረት ወይም ከክልል ስራ ቡድኖች በወቅቱ የሥራ ዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ያስገመግማል ተገቢውን ግብረ-መልስ ይሰጣል፤

8) ለክልል ፍልሰት ምክር ቤት ሊቀርቡ የሚገባቸውን አጀንዳዎች ለይቶ በአጀንዳነት እንዲያዝ ያደርጋል፤

9) የክልላዊ ምክር ቤቱ እና የትብብር ጥምረት ውሳኔዎች ተግባር ላይ እንዲውል ለሥራ ቡድኖች አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

10) ለጥምረቱ አባላት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣ መደበኛና ልዩ ስብሰባዎችን ያዘጋጃል፤

11) የትብብር ጥምረቱን እቅድና ሪፖርት ለምክር ቤቱ እና ለክልላዊ ትብብር ጥምረት ይልካል፤

12) ለትብብር ጥምረቱ መድረኮች የሚሆን ቴክኒካዊ ዝግጅቶችን ያስተባብራል፤

13) ለትብብር ጥምረቱ ስራዎች ዝግጅት የሚሆን ሰነዶችን ያዘጋጃል፤

14) ትብብር ጥምረቱ ሰብሳቢ እና ለሚመለከታቸው የሥራ ቡድን ሰብሳቢዎች ለተለያዩ ስራዎች የሚሆን የፋይናንስ እቅዶችን አዘጋጅቶ ያቀርባል ያስተባብራል፤

15) በዚህ አንቀጽ ከ1 እስከ 7 የተደነገጉ ድንጋጌዎች በየደረጃው በተቋቋሙ የትብብር ጥምረት ጽህፈት ቤቶችም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

16) ሌሎች በሰብሳቢው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 23. በየደረጃው የሚገኝ የትብብር ጥምረት ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

በየደረጃው የሚገኝ ጽህፈት ቤት የሚከተለው ተግባር እና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1) ክልላዊ ትብብር ጥምረት የሚሰጡ ውሳኔዎች እና አቅጣጫዎች ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

2) በየደረጃው የትብብር ጥምረት ስራዎችና ስብሰባዎች ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን የማስተባበር ሚና ይወጣል፤ ስብሰባዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው እንዲጠሩ ይከታተላል፤

3) የትብብር ጥምረቱን ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ እና ሌሎች መረጃዎችን ይይዛል፤

4) በዚህ ደንብ መሰረት ለትብብር ጥምረት የተሰጡ ተግባራትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

5) የትብብር ጥምረቱ ተሳታፊዎች በሚደረጉ ስብሰባዎችና ሌሎች መድረኮች በአግባቡ እየተሳተፉ ስለመሆኑ ክትትል ያደርጋል፤

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

6) በአግባቡ የማይሳተፉ ሲኖሩ ለትብብር ጥምረቱ ሰብሳቢ በማሳወቅ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
7) በየደረጃው ከሚገኙ ትብብር ጥምረት በወቅቱ የሥራ ዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ያስገመግማል ተገቢውን ግብረ-መልስ ይሰጣል፤
8) በየደረጃው ለሚገኙ ትብብር ጥምረት ሊቀርቡ የሚገባቸውን አጀንዳዎች ለይቶ በአጀንዳነት እንዲያዝ ያደርጋል፤
9) በየደረጃው የሚገኙ የትብብር ጥምረት ውሳኔዎች ተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
10) ለጥምረቱ አባላት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣ መደበኛና ልዩ ስብሰባዎችን ያዘጋጃል፤
11) የትብብር ጥምረቱን እቅድና ሪፖርት በየደረጃው ለሚገኝ ለበላይ ትብብር ጥምረት ይልካል፤
12) ለትብብር ጥምረቱ መድረኮች የሚሆን ቴክኒካዊ ዝግጅቶችን ያስተባብራል፤
13) ለትብብር ጥምረቱ ውይይት የሚሆን በቂ ዝግጅት ያደርጋል፤
14) ትብብር ጥምረቱ ሰብሳቢ ለተለያዩ ስራዎች የሚሆን የፋይናንስ እቅዶችን አዘጋጅቶ ያቀርባል ያስተባብራል፤
15) ሌሎች በሰብሳቢው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል።

### አንቀጽ 24. በየደረጃው ስለሚገኙ የትብብር ጥምረት አባላት መብት

ማንኛውም የትብብር ጥምረት አባል :-

1) አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ለትብብር ጥምረት ሰብሳቢ ሀሳብ ማቅረብ፤
2) ለስብሰባ አጀንዳ እንዲያዝላቸው የሚፈልጉትን ሃሳብ የማሳወቅ፤
3) በክልላዊ የትብብር ጥምረት ስብሰባ የመሳተፍና ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ፤
4) በክልላዊ የትብብር ጥምረት የሚተላለፉ ውሳኔዎችን የማወቅ መብት ይኖረዋል።

### አንቀጽ 25. በየደረጃው ስለሚገኙ የትብብር ጥምረት አባላት ግዴታ

ማንኛውም የትብብር ጥምረት አባል፡-

1) አዋጅን፣ ደንብን እና መመሪያዎችን የመደበኛ ስራው አካል አድርጎ የመፈጸም እና የማስፈጸም፤
2) የትብብር ጥምረት መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባ የመገኘት፤
3) በክልላዊ ምክር ቤቱ የወጡ መተዳደሪያ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እና አሠራር ሥርዓቶችን የመፈፀም እና የማስፈፀም፤
4) በምክር ቤቱ የተቀመጠውን አቅጣጫ እና ውሳኔ የመፈፀም እና የማስፈፀም፤
5) በትብብር ጥምረቱ ስብሰባ በምሥጢር እንዲጠበቁ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች የመጠበቅ፤
6) ሌሎች የትብብር ጥምረቱ የሚሰጡትን ተግባራት የመወጣት ግዴታ አለበት።

### አንቀጽ 26. የትብበር ጥምረት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

በየደረጃው የሚገኝ የትብብር ጥምረት የሚከተሉት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ይኖረዋል፡-

1) በየደረጃው የሚገኝ የትብበር ጥምረት በስድስት ወር እና በዓመት መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

2) ማናቸውም የትብበር ጥምረት ስብሰባ የትብበር ጥምረት አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

3) በየደረጃው የሚገኝ የትብበር ጥምረት ስብሰባ ውሳኔ የሚያልፈው በስብሰባው ከተገኙ የትብበር ጥምረት አባላት ከግማሽ በላይ ሲደገፍ ይሆናል፤

4) በስብሰባ ወቅት ድምፅ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሃሳብ የትብበር ጥምረት ውሳኔ ይሆናል፤

5) የትብብር ጥምረት አካል የሆኑት እያንዳንዱ የሥራ ቡድኖች በየሶስት ወሩ የሚሰበሰቡ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

### የሥራ ቡድኖች አደረጃጀት፣ አባል ተቋማት እና ተግባርና ኃላፊነት

**አንቀጽ 27. የሥራ ቡድኖች አደረጃጀት**

በትብብር ጥምረቱ ሥር የሚከተሉት የሥራ ቡድኖች ይኖራሉ፡-

1) የግንዛቤ ፈጠራ፣የባህሪይ ለውጥ እና የውጭ ሀገር ሥራ ሥምሪት የሥራ ቡድን፣

2) የወንጀል መከላከል እና የህግ ማስከበር የሥራ ቡድን፤

3) የጥናትና ምርምር የሥራ ቡድን፤

4) የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የሥራ ቡድን፤

5) የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን፤

6) የዲያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የሥራ ቡድን፤

7) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 6 የተጠቀሱ የሥራ ቡድኖች እንዳሉ ሆነው የክልላዊ ትብብር ጥምረት እንደ አስፈላጊነቱ ቁጥራቸውን ሊያሻሽል ይችላል፤

8) የሚመለከተው ተቋም የሥራ ዘርፍ ኃላፊ ወይም ተወካይ የሥራ ቡድን አባል ነው፤

9) ተቋማት በተለያዩ የሥራ ቡድኖች ዉስጥ ተሳታፊ መሆናቸው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሁለትና ከዚያ በላይ የሥራ ዘርፍ ኃላፊዎችን ሊወክሉ ይችላሉ፤

10) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ መሳተፋቸው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዋናው የትብብር ጥምረት ስብሰባ ጭምር እንዲገኙ ሊደረግ ይችላል፤

11) የሥራ ቡድኖች አደረጃጀት በትብብር ጥምረት ስር በክልል፣ በዞን፣ በከተማ አስተዳደር እና በወረዳ ላይ የሚደራጅ ይሆናል፤

12) የሥራ ቡድኖች ተጠሪነታቸው በየደረጃው ለሚገኙ የትብብር ጥምረት ይሆናል፤

13) የሥራ ቡድን አባል ተቋማት በየወሩ ለቡድኑ ሰብሳቢ ሪፖርት የሚያቀርቤ ይሆናል፤

14) የቡድኑ ሰብሳቢ በሶስት ወር አንድ ጊዜ የጋራ ውይይት መድረክ ያዘጋጃል ግብረ መልስ ይሰጣል፤

15) የቡድኑ ሰብሳቢ በየሶስት ወሩ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በየደረጃው ለሚገኝ ትብብር ጥምረት ጽ/ቤት የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

አንቀጽ 28.የግንዛቤ ፈጠራ እና የግንዛቤ ለውጥ የሥራ ቡድን አባል ተቋማት

የግንዛቤ ፈጠራ፣የባህሪይ ለውጥ እና የውጭ ሀገር ሥራ ሥምሪት የሥራ ቡድን የሚከተሉት አባል ተቋማት ይኖሩታል፡-

1) የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ……..ሰብሳቢ
2) የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ…….ፀሐፊ
3) የትምህርት ቢሮ……….አባል
4) ሰላምና ጸጥታ ቢሮ……….አባል
5) የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ……….አባል
6) የባህልና ቱሪዝም ቢሮ……….አባል
7) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ……….አባል
8) የጤና ቢሮ……….አባል
9) የደቡብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት……….አባል
10) ኢንቨትመንት ቢሮ……….አባል
11) የክልሉ የሐይማኖት ተቋማት ጉባዔ ……….አባል
12) የክልሉ ማህበራዊ አደረጃጀት ተወካይ……….አባል
13) በጎ አድራጎት ድርጅቶች……….አባል

አንቀጽ 29. የግንዛቤ ፈጠራ እና የባህሪይ ለውጥ የሥራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

1) ስለ ፍልሰት ምንነት፣ስላሉት አዎንታዊና አሉታዊ ጎኖች እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ይሰራል፤
2) ዜጎች በሃገራቸው ሰርተው መለወጥ እንደሚችሉ የማስገንዘብ ሥራ ይሰራል፤ በአካባቢያቸው ስላሉ እድሎች የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ይሰራል፤
3) ውጭ ሀገር ሄደው መስራት ለሚፈልጉ ዜጎች ስላሉ ህጋዊ አማራጮች ግንዛቤ ይፈጥራል፤
4) ግለሰቦችን እና ሌሎችን ባሳተፈ መልኩ ማህበረሰቡ የችግሩን መንስኤ እንዲያውቅና እንዲለይ፣የመፍትሄውም አካል እንዲሆን በማድረግ አሳታፊነት ያላቸው የመለተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች የሥራ እድል እንዲፈጠር ከፍልሰት ተመላሾችና የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የሥራ ቡድንና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤
5) የሀይማኖት አባቶችን፣የሀገር ሽማግሌዎችን፣ታዋቂ ማማሪያና የባህሪ ለውጥ መፍጠሪያ የማህበረሰብ ወይይቶች እንዲመቻቹ ያደርጋል፣ ይደግፋል፤
6) ከፍልሰት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ የኪነጥበብ ውጤቶችን በመጠቀም ለማህበረሰቡ ትምህረት እንዲሰጥ ያደርጋል፤ የችግሩን አስከፊነት የሚያብራሩ የተለያዩ በራሪ ወረቀቶችን በማዘጋጀት ለተደራሾች ያሰራጫል፤ የአደደባባይ ማስታዎቂያዎችን (ቢልቦርዶችን)በመትከልና ሌሎች መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም አስተማሪ መልዕክቶችን ያስተላልፋል፤

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

7) የመንግስትና የግል መገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም ስለ ፍልሰት ጉዳዮች ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን፣ዘገባዎችንና ሌሎች ስራዎችን ለህዝብ ተደራሽ ያደርጋል፤

8) ዜጎች ስለ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ፍልሰት በተለይም ከፍልሰት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በመጸየፍ በመልካም ሥነምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ለማስቻል በትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመሳተፍ የማማሪያ መድረክ እንዲፈጠርላቸው ክትትል ያደርጋል፤

9) አስተማሪ የሆኑ የሀገራችን እና የሌሎች ሀገራት ዜጎችን የፍልሰት ተሞክሮ በመቀመር የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ይሰራል፤

10) እንደአስፈላጊነቱ ከጥናት ክትትልና ግምገማ የሥራ ቡድን ጋር በመቀናጀት አስተማሪ ጽሁፎችን ያዘጋጃል፤በተሰሩ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች ስለ አስገኙት የባህርይ ለውጥ የዳሰሳ ጥናት ያደርጋል። ችግሮችን በመለየት ተግባራዊ ምላሽ ይሰጣል፣እንዲሰጥም ያደርጋል፤

11) የውጭ ሃገር ስራ ስምሪት የህግ ማእቀፎችና ስምምነቶች በትክክል ስራ ላይ እንዲውሉ ይሰራል፤

12) ተጎጂ ለሆኑ ዜጎች ከተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የሥራ ቡድን እንዲሁም ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ ድጋፎች እንዲያገኙ ይሰራል፤ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይሰራል፣ያስተባብራል፤

13) ወደ ውጭ ሃገር ህጋዊ ስራ ለመሰማራት የሚፈልጉ ዜጎችን ትምህርት ማስረጃቸውን ትክክለኛነቱን ያጣራል ያረጋግጣል፤

14) ሌሎች መሰል ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 30.የወንጀል መከላከል እና የህግ ማስከበር የሥራ ቡድን

የወንጀል መከላከል እና የህግ ማስከበር የሥራ ቡድን እንደ አስፈላጊነቱ ወደፊት ሊሳተፉ የሚችሉ ሌሎች ተቋማት የሚኖሩት ሲሆን የዚህ ቡድን አባል ተቋማት፦

1) ፍትህ ቢሮ…………..ሰብሳቢ
2) ፖሊስ ኮሚሽን …….ፀሐፊ
3) ሰላምና ጸጥታ ቢሮ……. አባል
4) የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጄንሲ…. አባል
5) የፍትህ አካላት ስልጠናና ምርምር ተቋም….. አባል
6) መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ………. አባል

አንቀጽ 31. የወንጀል መከላከል እና የህግ ማስከበር የሥራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

1) በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር ሲያቋርጡ የተገኙ ዜጎችን ወደ ክልሉ ሲመለሱ በማቆያ ጣቢያዎች እንዲቆዩ ያደርጋል። እነዚህንም ለመከላከል እና የተጎጅዎች ድጋፍና ማቋቋም ቡድን በማሳወቅ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

2) ህብረተሰቡ በፍልሰት ጉዳይ የወጡ ህጎችን እንዲገነዘብ ያደርጋል፤ተጎጂዎች ያላቸውን ልዩ መብት እንዲያውቁ ያደርጋል፤

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

3) የተጎጂዎችን መብት ማዕከል ያደረገ የተጠናከረና የተቀናጀ የድንበር ቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤
4) የወንጀል መከላከል እና የህግ ማስከበር ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተሻለ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲኖር ይሰራል፤
5) የህግ ማስከበር ስራውን ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ያዘምናል፤
6) የወንጀል መከላከልና የህግ ማስከበር አሰራሮችን ለማሻሻል የሚያስችሉ የህግ አስከባሪ ባለሙያዎችን አቅም የማጎልበት ስራ ይሰራል፤
7) ሌሎች መሰል ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 32.የጥናትና ምርምር የሥራ ቡድን

የጥናትና ምርምር የሥራ ቡድን ወደፊት እንደ አስፈላጊነታቸው የሚካተቱ አባላት የሚኖሩ ሲሆን ቡድን አባል ተቋማት፡

1) የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ተቋም ……..ሰብሳቢ
2) ትምህርት ቢሮ ……..ጸሐፊ
3) ደቡብ ክልል ውስጥ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች…….አባል
4) ፕላንና ልማት ቢሮ…..አባል
5) የፍትህ አካላት ስልጠናና ምርምር ተቋም…..አባል

አንቀጽ 33. የጥናትና ምርምር የሥራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

1) የሕገ-ወጥ ፍልሰት መስፋፋት መንስኤዎች፣ወንጀሉ ያለበት ደረጃና ተያያዥ ጉዳዮች አስመልክቶ ጥናት ያደርጋል ይህንንም ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤
2) ሕገ-ወጥ ፍልሰትን ለመከላከል የሚረዱ ስትራቴጅዎችን፣እቅዶችንና የድርጊት መርሀ ግብሮችን ያዘጋጃል፤
3) ሕገ-ወጥ ፍልሰትን በመከላከል ረገድ በክልል አቀፍ ደረጃ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ላይ ክትትል፣ድጋፍና ግምገማ ያደርጋል ለዚህም የሚረዳ ስርአት ይዘረጋል፤
4) ከፌደራልና ከሌሎች ክልሎች የልምድ ልውውጥ በማድረግ ተሞክሮ ያሰፋል።

አንቀጽ 34. የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የሥራ ቡድን

የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የሥራ ቡድን ወደፊት እንደ አስፈላጊነታቸው የሚካተቱ አባል ተቋማት የሚኖሩ ሲሆን የቡድን አባል ተቋማት፡-

1) ሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራዝ ልማት ቢሮ……….ሰብሳቢ
2) አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ………ፀሐፊ
3) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ….አባል
4) የከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ….አባል
5) ፋይናንስ ቢሮ……..አባል
6) ፕላንና ልማት ቢሮ……….አባል

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

7) ጤና ቢሮ……….አባል
8) ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ……….አባል
9) ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ…………..አባል
10) የኢትዮጲያ ቀይ መስቀል ማህበር ደቡብ ቅርንጫፍ……አባል
11) የደቡብ ክልል የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ……….አባል
12) የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ……….አባል
13) ዓለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅቶች……….አባል

አንቀጽ 35.የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የሥራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

1) ተጎጅዎችን በኢኮኖሚ፣በጤና፣በስነ-ልቦናና በማህበራዊ ህይወት ጉዳዮች የመደገፍና የማቋቋም ስራ ይሰራል፤
2) ድጋፍ ሊያገኙ የሚገባቸውን ተጎጅዎች የመለየት ስራ ይሰራል፤ለዚህም ይረዳ ዘንድ ድጋፍ የሚሹ ተጎጅዎችን መለያ መለኪያ (Victims Referral Standards) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያወጣል፤
3) ክልላዊ የተጎጂዎች ቅብብሎሽ ስርዓት ይዘረጋል፣ያስተባብራል፤
4) ተጎጂዎችን በሚመለከት የአሰራር ስርዓቶችን በማዘጋጀት ተጎጂዎች የሚደገፉበትን ስርዓት ይዘረጋል፣ በወጡ ህጎች አተገባበርም ላይ ክፍተቶችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ሀሳብ ያቀርባል፤
5) አገልግሎት ሰጪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መካከል የተቀናጀ የተጎጂዎች አገልግሎት አሰጣጥና ቅብብብሎሽ እንዲኖር ያስተባብራል፤
6) ተጎጂዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት የግል ዘርፉን ሳትፋል፣ያስተባብራል።
7) ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፣ያስተባብራል፤
8) ሌሎች መሰል ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 36.የዳያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የሥራ ቡድን አባላት

የዳያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የሥራ ቡድን አባላት ወደፊት እንደ አስፈላጊነታቸው የሚካተቱ አባል ተቋማት አባላት የሚኖሩ ሲሆን የቡድን አባል ተቋማት፡-

1) የዲያስፖራ፣አጎራባች ክልሎች ተሳትፎ እና ፕሮቶኮል ጉዳዮች ጽ/ቤት…….ሰብሳቢ
2) ኢንቨስትመንት ቢሮ……….ፀሐፊ
3) ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ……..አባል
4) ሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ………አባል
5) ባህልና ቱሪዝም ቢሮ……….አባል
6) የደቡብ ኢትዮጲያ ዳያስፖራ ማህበር……….አባል
7) ፍትህ ቢሮ……….አባል
8) በክልሉ የተደራጁ የነጋዴዎች ማህበር……….አባል

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

አንቀጽ 37.የዳያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የሥራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

1) የዳያስፖራ አባላትን በሀገራቸው የልማት ጉዳይ በተለይም የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ከማሳደግ፤በኢንቨስትመንት መስክ እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ በያገባኛል ስሜት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታዎች መዘርጋታቸውን ይከታተላል፤
2) ከዳያስፖራው የሚገኙ የእውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እድሎችን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፤
3) የግብረሰናይና የልማት ማህበራትን በኢትዮጵያ የልማትና ሌሎች ጉዳዮች ላይ እንዲያግዙ ያተጋል፤
4) የዳያስፖራው ማህበረሰብ ባህላቸውንና ታሪካቸውን የሚያውቁበትና የሚያዳብሩበት ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ይሰራል፣ያስተባብራል፤
5) የዳያስፖራው ማህበረሰብ ወቅታዊ ክልላዊ /ሀገራዊ/ ሁኔታዎችን እንዲከታተሉ በማንቃት /በማድረግ/ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና ገጽታ እንዲያስጠብቁ ይሰራል፤
6) ሌሎች መሰል ተግባራትን ይሰራል።

አንቀጽ 38.የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን አባላት

የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን አባላትወደፊት እንደ አስፈላጊነታቸው የሚካተቱ አባል ተቋማት የሚኖሩ ሲሆን የቡድን አባል ተቋማት፡-

1) የፕላንና ልማት ቢሮ ……….ሰብሳቢ
2) ፖሊሲ ጥናትና ምርምር እንስቲትዩት………..ፀሐፊ
3) ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ………….አባል
4) ፍትህ ቢሮ……………አባል
5) የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ……………አባል
6) የወሳኝ ኩነቶች አጀንሲ……………አባል
7) የዲያስፖራ፣አጎራባች ክልሎች ተሳትፎ እና ፕሮቶኮል ጉዳዮች ጽ/ቤት……አባል
8) ፖሊስ ኮሚሽን……………አባል
9) አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን……………አባል
10) ትምህርት ቢሮ……………አባል
11) ኢንቨትመንት ቢሮ……………አባል
12) የዓለም አቀፉ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ተወካይ……………አባል
13) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት ……………አባል

አንቀጽ 39.የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

1) ከፍልሰት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካላት በመሰብሰብ የተሟላና ወጥ የሆነ ክልላዊ የፍልሰት መረጃ ቋት ያደራጃል፣ይተነትናል፣ያስተዳድራል፤ እንደአስፈላጊነቱ ለህዝብ ተደራሽ ያደርጋል፤
2) አግባብነት ባላቸው አካላት ሲጠየቅም መረጃ ይሰጣል፤

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

3) የተቀናጀ የፍልሰት መረጃ ልውውጥ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል እንዲሁም
4) ሌሎች መሰል ተግባራትን ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 40.የሥራ ቡድኖች የአሰራር ስርዓት

1) የሥራ ቡድኖች ከትብብር ጥምረት ጋር የሚጣጣም የየራሳቸው ዕቅድ ይኖራቸዋል፤
2) የሚወጣው ዕቅድም የየተቋማቱን የሥራ ድርሻ በግልፅ መለየት የሚኖርበት ሲሆን በጋራ ሊሰሩ የሚገቡ ስራዎች ካሉ ይኸው ተለይቶ መቀመጥ ይኖርበታል፤
3) የሥራ ቡድኑ ተሳታፊ ተቋማትም የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ በመውሰድ በተቋማቸው ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤
4) የሥራ ቡድኖች የሴቶች፣ ህጻናት፣ የአዕምሮ ህመምተኞች እና የአካል ጉዳተኞችን ለአደጋ ተጋላጭነትና ልዩ ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ተግባርና ሀላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፤
5) የሥራ ቡድኖች ስራቸውን በተቀናጀና በተናበበ መልኩ መስራት የሚጠበቅባቸው ሲሆን የሥራ ቡድኑ ተሳታፊ ተቋማት የተሰሩ ስራዎችን ለቡድን ሰብሳቢ ተቋማት በየወሩ ሪፖርት ያደርጋሉ፤በየሶስት ወሩ በመገናኘት በቀረበው ሪፖርትና እየተሰሩ ባሉ ስራዎች ላይ ውይይት ያደርጋል፤
6) ቡድን ሰቢሳቢ ተቋምም ወቅቱን የጠበቀ የሶስት ወር፣የስድስት ወር እና በዓመት ሪፖርት ለትብብር ጥምረት ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

አንቀጽ 41. የሥራ ቡድን ሰብሳቢዎች ሚና

1) የየቡድን ሰብሳቢዎች የሰራ ቡድኖችን መደበኛ ስብሰባ በተቋማቸው ወይም በሌላ አመቺ ቦታ እንዲካሄድ ያስተባብራሉ፤
2) የቡድን አባላትን የሥራ ሪፖርት ተቀብለዉ በማጠናቀር ትብብር ጥምረት ጽ/ቤቱ በየሩብ ዓመቱ ወይም በተጠየቀው ጊዜ ይልካሉ፤
3) ሰብሳቢው ለስብሰባዉ የሚሆን የበጀት ከቡድኑ አባል ተቋማት ጋር በመቀናጀትና በማስተባበር ይፈልጋል ሲገኝም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

አንቀጽ 42. ስለእውቅናና ማበረታቻ

ተግባርና ሃላፊነታቸውን በአግባቡ የተወጡ የትብብር ጥምረት አባል ተቋማት እና ቡድኖች ተለይተው በየስብሰባ መድረኮች ላይ በይፋ እንዲታወቁ ይደረጋል፤ እውቅናና ማበረታቻ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

አንቀጽ 43. ተጠያቂነት

1) የትብብር ጥምረቱ አባል ተቋማት ለሥራ ቡድን ሰባሳቢ ተቋማት የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጡ በትብብር ጥምረቱ አማካኝነት ማስተካከያ እርምጃ በጽሑፍ ይሰጣል፤
2) በዚህ ደንብ መሰረት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በማይወጡ የሥራ ቡድን አባል ተቋም በሥራ ቡድን ሰባሳቢ አማካኝነት ማስተካከያ እርምጃ በጽሑፍ ይሰጣል፤
3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ኃላፊነታቸውን የማይወጡ ተቋማት በዝርዝር ተለይተው በትብብር ጥምረትና በሥራ ቡድን ስባሰባዎች ላይ እንዲታወቁ ይደረጋል፤

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

4) አባል ተቋማት የመደቧቸው ተወካዮች በአግባቡ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ በየተቋማት የውስጥ አሰራር መሰረት ተጠያቂ ይደረጋሉ፤ በቦታው ሌላ ተወካይ እንዲተካ ይደረጋል፤

5) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 4 መሰረት ማስተካከያ ካልተደረገ የትብብር ጥምረቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለክልል ፍልሰት ፍልሰት ምክር ቤት ሪፖርት ያደርጋል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 44. የመተባበር ግዴታ

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት።

### አንቀጽ 45.የማስፈጸም ግዴታ

ማንኛውም አባል ተቋማት ክልላዊ ምክር ቤት እና የትብብር ጥምረት ጽ/ቤት የሚመለከቱ ተግባራትን በአግባቡ የመፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ አለበት።

### አንቀጽ 46.መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ክልላዊ ምክር ቤቱ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

### አንቀጽ 47. ደንቡን ስለማሻሻል

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ይህንን ደንብ ሊያሻሽለው ይችላል።

### አንቀጽ 48. ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የላቸውም።

### አንቀጽ 49. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከፀደቀበት——ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ወላይታ ሶዶ

ሐምሌ 6 ቀን /2፻፲7 ዓ/ም

ጥላሁን ከበደ

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)